ሳምንታዊ ዜና (ነሐሴ 17 ቀን 2000 ዓ. ም.)

በቤተክህነት ውስጥ ሽኩቻ መኖሩ ተነገረ፣ 4 ጳጳሳት አባ ገ/መድህንን አውግዘው ሰባኤ ገቡ፣ 13 ሚሊዮን ሕዝብ ለረሀብ አደጋ መጋለጡ ተገለፀ፣ የወያኔ ባለሥልጣናትም ሕዝቡ በችግር ካለቀ በሁዋላ ረሀቡ ተከሰተ ሲሉ መጮህ ጀመሩ፣ ለወያኔ ካድሬዎች የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ፣ እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን በወያኔ ፖሊሶች በደርሰበት ጫና ምክንያት ለሕመም ተዳረገ፣ በቃሊቲ ውስጥ ዞን አምስት ተብሎ ወደ ሚጠራው ክልል ተዛወረ፣ ወደ ሐኪም ቤት እንዳይሄድ፣ ሐኪምም እንዳይገባ ተከለከለ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ........................

የወያኔው ቀደኛ ካድሬ ሆኖ እያገለገለ ያለው አባ ገ/መድህን በሚመራው ቤተክህነት ውስጥ ከፍተኛ ሽኩቻ መጀመሩን የቤተ ክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በአባ ገብረመድህን እና በጳጳሳት መካከል የተከሰተው ይኸው ክፍፍልና ሽኩቻ ከተጀመረ የቆየ ቢሆንም በቅርቡ ግን ነገሮች እየተለዋወጡ ወደ አተካሮ ማምራታቸውን የገለፁት ምንጮች አባ ገ/መድህን የእምነት አባትነት ቅንጣት ታክል በውስጡ የሌለ ከመሆኑም በላይ ፍፁም የካድሬነትና የነጋዴነት ስራ አጉልቶ እያወጣ በመሆኑ ለእምነት የሚቆረቆሩ ጳጳሳት ድርጊቱን እያገወዙ መሆናቸውን ምንጮቹ አጋለጡ::

ለመጓጓዣ ጥይት የማይበሳው መኪና ከመግዛት ጀምሮ እስከ ጮማና ውስኪ ድረስ ከፍተኛ ወጭ የሚያወጣው አባ ገ/መድህን ፍፁም የእምነት አባትነት በውስጡ የሌለ ከመሆኑም ባሻገር እርሱም እንደ ሌሎቹ የወያኔ ካድሬ ባለሥልጣናት የሀብት ማከማቸት ስራ ላይ ተጠምዶ በመገኘቱ አብረውት ባሉ ጳጳሳት ከፍተኛ ትችትና ወቀሳ እየተሰነዘረበት እንደሚገኝ ምንጮቹ አብራርተዋል::

ከዚህ ቀደም ሁሉንም ነገር በስውር ይፈፅም የነበረውና የወያኔ ካድሬ ሆኖ እያገለገለ ያለው አባ ገ/መድህን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ጌታውን መለስንና ስርዓቱን በመተማመን ከሕዝበ ክርስቲያን በሚሰበስበው ገንዘብ ከፍተኛና ግዙፍ የንግድ ተቋማትን ከሌሎች ነጋዴዎች ጋር በመሻረክ እየሰራ እንደሚገኝ የገለፁት ምንጮቹ በተለይም በኮንስትራክሽን ድርጅት፤ በፋብሪካና በሌሎችም የንግድ ተቅዋማት ውስጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሚገኝም አጋልጠዋል::

ይህንን ሁኔታ የተረዱት ለእምነታቸው የፀኑ 4 ጳጳሳት አባ ገ/መድህንን በመቃወም ከአንድም ሁለት ሶስቴ በአቡነ ገሪማ በኩል ቢመክሩና ቢቆጡም ጥሩ ምላሽ ያላገኙ ከመሆኑም በላይ በአባ ገ/መድህንና ደህንነቶቻቸው ጥርስ የተነከሰባቸው ሲሆን፣ ይህ ጉዳይ በቤተክህነት ውስጥ ጎልቶ በመውጣቱና በመታወቁ በሁለት ጐራ ተከፍለው ሽኩቻ ቢጀመርም ሰውየው በደህንነቶች አማካኝነት ጉዳዩን ሊያፍ እንደቻለም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ከአንድ የሀገር መሪ ፖለቲከኛ በላይ በፌዴራል ፖሊስ የሚጠበቀው አባ ገ/መድህን በቤተክህነት ግቢ ውስጥና በመኖሪያው ውስጥ የፌዴራል ፖሊስ ሰፍሮ ጥበቃ ከማድረጉም በላይ ወደ ቢሮው የሚገባ ማንኛውም ጳጳስ ተፈትሾ እንዲገባ ትዕዛዝ መስጠቱን ያጋለጡት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ድርጊቱ ከአንድ የእምነት አባት ነኝ ከሚል ሰው የማይጠበቅ በመሆኑ ይህንኑ ስህተት እንዲያርም ጳጳሳቱ ቢጠይቁም አሻፈረኝ በማለቱ አራት ጳጳሳት ሱባኤ መግባታቸውን አስረድተዋል::

ከፀሎት ይልቅ ሙዚቃን፣ ከሀዘን ይልቅ ደስታን ፤ ከጥሬ ቆሎ ይልቅ ጮማን፣ ከውሃ ይልቅ ውስኪን የሚመርጠው አባ ገ/መድህን ወያኔ በረሀ እያለ አሜሪካን ሀገር ከቤተክርስቲያን ከሚገኘው ገንዘብ በመሰብሰብ በረሀ ድረስ ሲረዳ እንደነበረና ወያኔ ስልጣን ላይ ሲወጣ ለዋለው ውለታና ከአድዋ ተወላጅነቱ ጋር ተዳምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መሪ ሆኖ ቀኖና እና የቤተክርስቲያን ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ የፖለቲካ ተሿሚ ሆኖ ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሕዝበ ክርስቲያን የሚሰበሰበውን እና በክርስትና እምነት አማኞች ስም ተለምኖ የሚመጣውን ገንዘብ በራሱ የግል ሒሳብ ስም እየከተተ ከፍተኛ ሀብት ያከማቸ ከመሆኑም በላይ ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ አላቸው ከተባሉት ባለሀብቶች በላይ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርቶ መገኘቱ ያበገናቸው የእምነቱ አባቶች ሰሞኑን ሱባኤ መግባታቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ይኸው በቤተክህነት ውስጥ የተጀመረው ሽኩቻ ተጋግሎ ሊፈነዳ በተቃረበበት ወቅት በሰልጣኝ ካባ ለባሽ ደህንነቶች ሊከሽፍ እንደቻለ የጠቆሙት ምንጮቹ ሰሞኑን ደግሞ የወያኔው መሪ መለስ በከፍተኛ ችግር ላይ ስለሆንን ያላችሁን ገንዘብ አውጡና ስጡን ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተነሳ አባ ገ/መድህንም የአለቃውን የመለስን ትዕዛዝ ለመፈጸም ከየቤተክርስያኑ ሙዳየ ምፅዋት ተገልብጦ ይምጣልኝ በማለቱ ተጀምሮ የነበረው ግጭት ተካርሮ እንደነበር ገልጸዋል:: ምንጮቹ አሁንም በግቢው ውስጥ ጥሩ ድባብ ያልሰፈነበት፣ ከእምነት ቦታ ይልቅ የፖለቲካ ስራ የሚሰ[illegible]በት ግቢ ሆኖ መገኘቱ በእጅጉ ለእምነቱ ተከታዮች አንገት የሚያስደፋና የሚያሳቅቅ ነው ሲሉ አብራርተዋል::

አባ ገ/መድህንም ከመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መጠኑ ያልታወቀ ከየቤተክርስቲያኑ በግል ሒሳብ ደብተሩ የገባውን ገንዘብ የሰጠ መሆኑንና ብዙዎቹ ቤተ ክርስቲያናት (ደብሮች) የየራሳችንን ስራ እያከናወንንበት በመሆኑ ገንዘብ የለንም የሚል ምላሽ እየሰጡ መሆናቸው ያበሳጫቸው መሆኑንም ምንጮቹ ዘግበዋል::

በደርግ ስርዓት አራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ታስሮ በነበረበት ጊዜና በተለይም አሜሪካ ሆኖ ገንዘብ እያሰባሰበ ለጦርነቱ ከፍተኛ ድጋፍ በማድረጉ የተነሳ ውለታውን ለመመለስ ሲባል የቤተክርስቲያን ሕግና ደንብ ከሚፈቅደው ውጭ ወያኔዎች ከአሜሪካ አምጥተው የእምነቱ አለቃ ማድረጋቸው

የሚታወቅ ሲሆን፣ ቀድሞ ወያኔዎች በረሀ በነበሩበት ጊዜ ከሚያገለግለው በላይ በአሁን ሰዓትም በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ረገድ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ምንጮች አጋልጠዋል::

ዛሬ በሀገሪቱ የረሀብተኛ ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እያሻቀበ በሚሄድበት ወቅት አንድም ቃል ትንፍሽ ያላለው አባ ገ/መድህን ይልቁንም ከሕዝቡ አፍ እየነጠቀ ለሰው ልጆች ማለቂያ ለሆነው ጦር መሣሪያ መግዣ እንዲሆን ከየቤተክርስቲያኑ እየለቃቀመ ለወያኔ መስጠቱ አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑም ባሻገር ሰውየው የፖለቲካ እንጂ የእምነት ሹመኛ አለመሆኑን ቁልጭ አድርጐ ያሳየ ነው ሲሉ እነኚሁ ምንጮች አስረድተዋል::

በሌላ በኩል ከ8 ወራት በፊት ረሀብ በሀገሪቱ ተከስቷል አስቸኳዋይ መፍትሄ ይፈለግለት እየተባለ ሲጮህ ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉት የወያኔ ባለሥልጣናት ሰሞኑን አዲስ የነጠላ ዜማ አውጥተው እየወተወቱ መሆናቸው በዲፖሎማቶች ዘንድ ትዝብት ላይ እንደወደቁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ::

በአጭሩና በእንጭጩ ሊቀጭ የሚችለውን ረሀብ ትኩረት ሳይሰጡት ይባስ ብለው ረሀብ መከሰቱን አረጋግጠው እርዳታ እንስጥ ያሉትን የአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የተለያየ ታፔላ እየለጠፉ ከሀገር ውስጥ እንዲወጡ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ እንግባ ያሉትንም ቢሆን እንዳይገቡ ሲከላከሉ የነበሩት እነዚሁ ሹመኛ ካድሬዎች ሰሞኑን የድረሱልን ጥሪ እያሰሙ መሆኑ የአለምን ሕዝብ ጭምር ያስገረመና ያስደነቀ መሆኑን ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

የሰው ልጅ በየቀየው፣ በየጐዳናው፣ በየመንገዱ ላይ እንደ ቅጠል እየረገፈ ባለበት ወቅት የሚሊኒየሙ በዓላችን ይበላሽብናል በሚል ብቻ በሀገሪቱ ረሀብ እንዳልተ ሰተ ደብቀው ይልቁንም ትርፍ አምራች አርሶ አደር በሀገሪቱ ፈጥረናል በማለት ብረት እያቀለጡ በመሸለም የአለምን ሕዝብ ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲፍጨረጨሩ የከረሙ ሲሆን ዛሬ ሁኔታው ተለውጦ ችግሩ ተባ ስቦና ተስፋፍቶ ሲመጣ የድረሱልን ጥሪ ማቅረባቸው አንድም ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ማስመሰያ ዘዴ ነው ያሉት እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ውሎ አድሮ ወደፊት ይህ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው ርሀብ ከተጠያቂነት የማያድናቸው መሆኑን ሊያውቁት ይገባል ሲሉም አስተያየታቸውን ሲሰጡ ተደምጠዋል::

አዜ ኃይለስላሴ የልደት በዓላቸውን ለማክበር ሲሉ ኬክ ከእንግሊዝ አስመጥተው ሲምነሸነሹ ረሀብተኛ ው ወገን ቁጥሩ በመቶ ሺህዎች ደርሶ እንደነበርና ደርግም 10ኛው የአብዮት በዓልን ለማክበር በብዙ ሚለዮን ብር የጦር መሣሪያ አስገዝቶ ትርኢት ሲያሳይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጐች በረሀብ እየተቆሉ እንደነበር ያስታወሱት አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ

መምህር ወያኔ ከሁለቱም ስርዓቶች በባሰ መልኩ ዘንድሮ ከ13 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በረሀብ እየሞተና እያለቀ መሆኑን ደብቆ ሚሊኒየም በዓልን ለማክበር በብዙ ቢ ዮን ብር በላይ ወጭ መድቦ ሲዝናና መኖሩ የሁሉም አምባገነን ስርዓቶች ግብአተ መሬታቸው የሚፈፀ ውና የስርዓቶቻቸው ማክተሚያ በርሀብ ችግር የተነሳ መሆኑን በግልፅ ያመላከተ ነው ሲሉ አብራርተዋል::

ሕዝቡ የዕለት ጉርስ ስጡኝ እያለ በችግር ተጠብሶ አይኑ እያየ ጆሮው እየሰማ ወደ መቃብር እየወረደ ባለበት በዚህ ወቅት እነ መለስ ዜናዊ ከሚስቶቻቸው ጋር የሚሊኒየም በዓል በሚል አስረሽ ምቺው ዳንኪራ በየመድረኩ እየረገጡ መሆናቸው በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑም ባሻገር በጌቶቻቸው ምዕራባውያን ዘንድም ከፍተኛ ትዝብት ላይ የወደ በት ወቅት ነው ሲሉ እኚሁ ምሁር በንዴት ገልፀዋል::

በአሁን ወቅት ከአዲስ አበባ ምዕራብ አቅጣጫ 100 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አምቦ አካባቢ ከ100 ሺህ ሕዝብ በላይ በከፍተኛ ረሀብ ውስጥ የሚገኙ ከመሆኑም በተጨማሪ በደቡብ፤ በኦሮሚያ፤ በአማራ፤ በአፋር፤ በሱማሌ፤በቤንሻንጉልና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ረሀብተኛ ወገኖች የሚገኙ ሲሆን በተለይ በዚህ ሰሞን ደግሞ የረሀብተኛው ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን እራሳቸው ረሀብ የለም ሲሉ የነበሩት የወያኔ ባለስልጣናት እየወተወቱ መሆናቸው  ዝብት ላይ ጥሎዋቸዋል ሲሉ እኚሁ ምሁር ተችተዋል::

ጦርነት እየጐሰመ ሕዝቡን ታጠቅ ዝመት እያለ የሚያቅራራው ወያኔ በረሀብ ሲቆላ አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንደልሰማ ፊቱን አዙሮ ሚሊኒየም በዓልን አከብራለሁ እያለ ሲለፍፍ መክረሙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ንቀትና ጥላቻ በግልፅ ያሳየ ነው ያሉት አንድ አባት ይህንን የመሰለ ግፍ በህዝብ ላይ የፈፀመ አውሬ ቡድን አዝሎ መጉዋዙ በእጅጉ ያሳፍራል ስለዚህ መፍትሄ ልንሰጠው ይገባል ሲሉ ተደምጠዋል::

ረሀብ፣ ችግርና ችጋር የኢትዮጵያን ሕዝብ እያንገላታው ባለበት በዚህ ወቅት በሀገሪቱ ከፍተኛ የመብራት ኃይል እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት በርካታ ፋብሪካዎች ሰራተኞቻቸውን ማባረራቸው ችግሩ ወደ ከፋ ሁኔታ እንዲሸጋገር ማድረጉ ተገለፀ::

ለጐረቤት ሀገሮች የሚበቃ ኃይል አለን እያለ ሲደነፋ የከረመው የወያኔ ቡድን ከጥር ወደ ጀምሮ መብራት በፈረቃ አድርጎት የከረመ ሲሆን የውሃ እጥረት ነው እያለ ሕዝብን ሲያታልል ቢከርምም አይነጋ መስሏት... እንዲሉ ክረምቱ ከገባም በኋላ የመብራት ስርጭት በመቋረጡ ምክንያት የውሃ ችግር ሳይሆን ከአቅም በላይ ለሱዳን መሸጡን የመብራት ኃይል ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

እውነት እሬቱ የሆነው  የወያኔ ቡድን  መብራት የሚጠፋው በውሃ  እጥረት ምክንያት የተከሰተ ነው እያለ ለብዙ ወራት ሕዝቡን ለማታለል  ሲዳክር የከረመ  ቢሆንም  የዝናብ  ወቅት ደርሶ  ውሀ ግድቡን ጥሶ  እየወጣ  ባለበት በአሁኑ ጊዜም  ቢሆን  መብራት  በአግባቡ ካለመድረሱ  በተጨማሪ የአዲስ አበባ  ከተ  የመንገድ  ላይ  መብራቶች ሙሉ በሙሉ  የተቋረጡ  መሆኑን የጠቀሱት የመብራት ኃይል  ምንጮች ቀድሞም በውሸት ላይ  የተገ ባው  ወያኔ  እንዲሁ ሲዘላብድ  ቆየ እንጂ የኃይል  አቅርቦቱ እጥረት የተፈጠረው  ለሱዳን በመሸጡ  ነው  ሲሉ  አጋልጠዋል::

የወያኔ ቡድን  በግፍ  ያለ ምንም ኃጢያቱ  ያሰረው እውቁ ድምፃዊ  ቴዎድሮስ ካሣሁን   ሰሞኑን መጠነኛ የጤና  መታወክ እንደደረሰበት   ከእስር  ቤት ምንጮች የተገኘው  ዘገባ ገለፀ::

እውቁ  ድምፃዊ  ከሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም  ወህኒ ከወረደበት  እለት  ጀምሮ  በወያኔ ቅጥረኛ የእስር  ቤት ፖሊሶች  የተለያየ ጫና እየደረሰበት መሆኑን  የጠቆሙት  ምንጮቹ በተለይም ሕዝቡ በፍርድ  ቤት  በሚያሳየው  ክብርና  አድናቆት  እየተናደዱ  አንዴ ለብቻው ሌላ ጊዜ ደግሞ  በአንድ ቤት  ከ400  በላይ በታሰሩበት ክፍል  እያስገቡ  እያሰቃዩት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መጠነኛ የጤና መታወክ እንደደረሰበት  አስረድተዋል::

ቴዲ በሚደርስበት  ከፍተኛ  ጫና የተነሳ  ለአእምሮ ጭንቀት  ሕመም  ሊዳረግ እንደቻለ የጠቆሙት ውስጥ  አዋቂ ምንጮች በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻውን  ግድግዳው በተበሳሳና  ጣራው  በሚያፈስ ክፍል  ውስጥ  አስረውት ሲያሰቃዩት  ከቆዩ  በሁዋላ  ሰሞኑን  ደግሞ  መልሰው ዞን  አምስት ተብሎ በሚጠራው ግቢ  ውስጥ  እንደከተቱት  ምንጮች  ገልፀዋል::

ሕመሙ እንዳይባባስበትና እንዲታከም ወይም በሕክምና ባለሙያ እንዲታይ ቢወተውትም  ከ10ኛ  ክፍል ያልዘለሉ  በረሽ  አመጣሽ  ሐኪሞች  በግቢው  ውስጥ ስላሉ እነሱ ዘንድ አቅርበው እያመላለሱ ይበልጡንም ሕመሙ እንዲባባስበት  እያደረጉት መሆኑንና ከእስር ቤት ወደ ውጭ  ወጥቶ ሳይካትሪስት ጋር እንዳይታይ  ወይም  ደግሞ  የሕክምና  ባለሙያው  ወደ  እስር  ቤት ገብቶ እንዳያየው መከልከሉ  ሆን  ተብሎ ቴዎድሮስን በጭንቀት  ሕመም  እንዲሰቃይ  ለማድረግ  ታስቦ  መሆኑን ምንጮቹ  ገልፀዋል::

የቃሊቲ እስርቤት፣  የዝዋይ እስር ቤት  እና  የድሬዳዋ  እስር ቤቶች በፌዴራል  ማረሚያ  ቤቶች አስተዳደር  ይተዳደራል  በሚል በረሀ  አመጣሽ የወያኔ  ታጋዮችን መድበው በእስረኞች ላይ  ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ  እንዲወስዱ  እየተደረገ  ሲሆን  በቃሊቲ  እስር  ቤት  ውስጥም  ከዋና  ኃላፊው እስከ ተራ ተላላኪ  ድረስ  የወያኔ አባሎች ብቻ በመሆናቸው የተነሳ በእስረኞች ላይ የግፎች ሁሉ  ግፍ እየተፈፀመባቸው  እንደሚገኝም  ምንጮቹ  ጠቁመዋል::

በዚህም የተነሳ   እውቁ ድምፃዊ በተለይ ከ1997 ዓ.ም ጋር ተያይዞ በተለቀቀው  ካሴቱ  ሲያርሩና ሲበግኑ የነበሩት  የወያኔ የእስር ቤት  ፖሊሶች በዚህ  አጋጣሚ  እጃቸው  የገባውን ቴዲ  አፍሮን

*በእስር ቤት ውስጥ እያንገላቱት ሲሆን፣ በዚህም ድርጊት እየተበሳጨ ለአእምሮ ሕመም መዳረጉን ምንጮቹ አስረድተዋል።*

*ከየትኛውም የፖለቲካ እስረኞች በላይ ዘመድ እንኩዋን እንደልቡ ገብቶ እንዳይጠይቀው ተደርጎ ነገ ለሚመጣው ዛሬ ስም አስመዝግብ ተብሎ እና ሁለትና ሶስት ጠያቂዎቹ ውጭ ሌላ እንዳይመጣ በመደረጉ ጭምር በመበሳጨት ለሕመም እንደተዳረገ የገለፁት ምንጮች ብቻውን ሲሆን ግጥም ሊጽፍ ይችላል በሚል ብዕር እንዳይገባለት የከለከሉት ሲሆን አሁን ደግሞ በአይነ ቁራኛ ለመጠበቅ እንዲያመች ዞን 5 ተብሎ የሚጠራው ክልል አስገብተውት እንደሚገኝ ምንጮች ገልፀዋል።*

*በተቀነባበረና በሀሰተኛ ክስ ለእስር የተዳረገው ቴዲ በሬ ካራጁ እንዲሉ በጠበቃው፤በዳኛው እና በአቃቤ ህጉ ምስጢራዊ ሴራ ነገሮች እየከረሩ ለዚህ በቅቷል ያሉት አንድ የሕግ ባለሙያ ይዋል ይደር እንጂ እውነቱና ሀቁ ወደፊት መውጣቱ አይቀሬ ነው ሲሉ ገልፀዋል።*

*የቴዲ አፍሮ እናት በልጃቸው መታሰር ደንግጠው ህክምናቸውን አቋርጠው ከውጭ ሀገር ተመልሰው ወደ ሀገር ቤት የገቡ ቢሆንም በቴዲ ላይ እየተሰራበት ያለውን ሸፍጥ ሲመለከቱ በመበሳጨታቸው የተነሳ የቀድሞ ሕመማቸው ተነስቶባቸው ሆስፒታል እንደከረሙ ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀው አሁንም በልጃቸው መታሰርና እዛ ውስጥ በሚደርስበት እንግልት የተነሳ ጧትና ማታ እያነቡ
እንደሚገኙም ገልፀዋል።*

*ዳኛውን ልዑል ገ/ማርያም ለዳኞች ዲስፒሊን ኮሚቴ እከሳለሁ። ሀሰተኛ ምስክርነት ቃሉን በሰጠው ኩባዊ ሐኪም ላይም የወንጀል ክስ እመሰርታለሁ እያለ ሲያቅራራ የነበረው ጠበቃ ተብየ የኢህአዴግ አባል ሚሊዮን አሰፋ ላይ የ50 ቀናት እስራት ተፈርዶበት በአንድ ቀን የተለቀቀ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በግለሰቡ ላይ ህዝቡ ከፍተኛ ጥርጣሬ አጭሮበት ይገኛል ያሉት የፍርድ ቤት ምንጮቻችን በተለይ በሀገሪቱ ታሪክ በሰዓታት ልዩነት ይግባኝ ታይቶ ከእስር መለቀቁ ጥርጣሬውን ሊያጎላው እንደቻለም ይገልፃሉ።*

*ሚሊዮን አሰፋ የተባለው የቴዎድሮስ ጠበቃ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ጋር ተያይዞ ከወያኔው ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ገንዘብ ተከፍሎት ጥብቅና የቆመ ሲሆን በቅርቡም የመገናኛ ብዙኃን ሕግ ሲረቀቅ ጀምሮ እስኪፀድቅ ድረስ ከሽመልስ ከማል እና ከበረከት ስምኦን ጋር በመሆን ለወያኔ ከፍተኛ ስራ የሰራ መሆኑን ገለጹት ምንጮቹ በቴዲ ላይ እየተሰራ ባለው ሴራ ምናልባትም እጁ ሳይኖርበት አይቀርም የሚሉ በርካታ የቴዲ አድናቂዎች ናቸው።ቴዲ ማስርጃዎቹን ይዞ እንዲቀርብ ለመስከረም 29 ቀን 2000 ዓ.ም ቀጠሮ እንደተሰጠው የሚዘነጋ አይደለም።*

*በአሁን ሰዓት የኑሮ ውድነት በከፍተኛ ደረጃ ስር የሰደደበት ወቅት በመሆኑ በእስር ቤት ውስጥ ላሉ እስረኞች በቀን ሁለት የበቆሎ ቂጣና ከውሃ የቀጠነ ሽሮ ጋር እንደሚሰጣቸውና በርካቶችም*

በሽታ መቋቋም አቅቷቸው ለአልጋ ቁራኛ ተዳርገው እንደሚገኙ ከተለያዩ እስር ቤት ውስጥ ከሚገኙ ምንጮች የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በመጨረሻም ወያኔ ለስልጣኔ ያሰጉኛል በሚል ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ንፁሃን ዜጎችን ከየጐዳናው ላይ እያፈሰ ወደ እስር ቤት እያጋዘ ባለበት በዚህ ወቅት ያገለግሉኛል ብሎ ላስቀመጣቸው ካድሬዎቹ ደግሞ ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ እያደረገ መሆኑን ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በቅርቡ ብቻቸውን ተወዳድረው አሸነፉ የተባሉት የወያኔ ሹመኛ ካድሬዎች አዲስ አበባ መስተዳድርን ከተረከቡ በኋላ ወዲያው የደመወዝ ጭማሪ በመጠየቃቸው ምክንያት ከፍተኛ ጭማሪ የተደረገላቸው መሆኑን የማዘጋጃ ቤቱ ምንጮች ዘገባ አስረድቷል::

ከከንቲባው ምርኮኛ ኩማ ደመቅሳ ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ላሉ ባለሥልጣናት ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ የተደረገላቸው መሆኑን የገለፁት ምንጮች ለከንቲባው ኩማ ደመቅሳ 5ሺህ ብር የወር ደመወዝ፣ 1500 ብር የቢሮ መጠባበቂያ1500 ብር ደግሞ ለነዳጅና ለሌሎች ጉዳዮች በሚል የተመደበለት ሲሆን፤ አራት መኪኖችም ለግሉ እንዲጠቀምበት መደረጉን ከምንጮቹ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል::

ሕዝቡ በረሀብና በችጋር እየተሰቃየ ለአንድ ወያኔ ሹመኛ ካድሬ ከ8ሺህ ብር በላይ በየወሩ ወጭ የተመደበለት ከመሆኑም ባሻገር ተራ ለቀበሌ ሊቀመንበር የወር ደመወዝ 2340 ብር ሲሆን፣ 1500 ብር አበል መመደቡንም ምንጮች አጋልጠዋል::

በሀገሪቱ የኑሮ ውድነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ የዕለት ጉርስ የሚቀምሰው አጥቶ በየጐዳናው ላይ እየወደቀ ባለበት በዚህ ወቅት ያለ አንዳች ይሉኝታና ማን አለብኝነት ለአዲስ ካድሬዎች ድልብ እና ሀገሪቱ መክፈል ከምትችለው በላይ ደመወዝ መመደቡ በእጅጉ የሚያሳፍር ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በንዴትና በብስጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በቅርቡ ስንዴ አንድ ኩንታሉ በ350 ብር ገበያ ላይ ይውላል እያለ የወያኔው መሪ ቢለፍፍም ማንንዣ ገንዘብ ካላመጣችሁ እህሉ አይመጣም በማለት ከሕዝቡ ላይ ሽማቾች ማህበር በሚል በተቋቋመው የወያኔ የአገዛዝ ስልት ገንዘብ እየሰበሰቡ መሆኑ ምንጮች ገልፀዋል::

አንድ ኩንታል ጤፍ 1400 ብር ፤አንድ ኩንታል ስንዴ 800 ብር እየተቸበቸበ ባለበት በዚህ ወቅት ወደ ሀገር ውስጥ ገባ የተባለው ስንዴ በዕርዳታ የተሰጠ መሆኑን ሁኔታውን የተከታተሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገልጸው መጣ የተባለው ስንዴም ጥራቱ እጅግ የወረደ ነው ሲሉም ተደምጠዋል::